IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

# AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 1
# AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1
# AMHARE A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1

Monday 19 May 2003 (morning)
Lundi 19 mai 2003 (matin)
Lunes 19 de mayo de 2003 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- Ne pas ouvrir cette épreuve avant d'y être autorisé.
- Rédiger un commentaire sur un seul des passages.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento.

**ከሚከተሉት ጽሑፎች አንዱን መረጠህ(ሽ) አስተያየትህን(ሽን) ስጥ(ስጪ)።**

1. (ሀ)

**ወርቅ ነው**

በእሳት ነበልባል ወርቅ እንደሚፈተን
መላ አካሉ ሲግም ጠባዩ እንደሚገን
ወርቃማው አካሉ ውስጣዊው ባሕርዩ ምንም ሳይለወጥ
በላንቃው ወላፈን በነዳጁ ረመጥ
በመከራው እሳት ያለፈው አካልም
ይጠራል እንደ ወርቅ አይበግንም አይከስልም
ላዕላዊ ቁመናው ቢለውጥም ቅሉ
የምግብ ውጤቱ ጠንካራው አካሉ
በነዳድ ነፋሱ የተለበለበው
የሱነቱ ሽፋን መልኩን የቀየረው
ቀንበር የከበደው
ሸክም ያጎበጠው
አካሉ ቢከስልም ሕሊናው ወርቅ ነው።
ሕሊናው ወርቅ ነው ሰብአዊ ሚዛኑ፤
መከራ የገራው የእሳት ፍትኑ
ከእሳቱ ሲወጣ ከሚንቦገቦገው
ነዲድ የፈተነው የጠራ ወርቅ ነው!
ያንጊዜ ይሆናል የአንጥረኞች ምርጫ
የክብር መለኪያ መዋቢያ ማጌጫ
ለሙሽሪት ጥሎሽ ድሪ ለአንገቷ
ለክናዱ አንባር፥ ቀለበት ለጣቷ
"ጨረቃ ጠልሰሚም" ይሠራል በወርቁ
አልቦዋ መስቀሉዋ ትንሹ ትልቁ
ሁሉም የሚመርጡት ንጹሕ የጠራ ወርቅ
ከነበልባል አፎት በሳት የሚላቀቅ!
ወርቅ ነው ንጹሕ ወርቅ ምርት የሚሆን ነዋይ
ከጨረቃ እሚደምቅ እሚያበራ እንደ ጣይ!

1980 ሶማሊያ (ሐዋይ)
ከዐሥራ አንድ ዓመት የእስር ዘመን
ከሶማሊያ ለተመለሱ ሁሉ

ከበደች ተክለአብ፥ <u>የት ነው?</u> 1983።

1. (ለ)

“ ለተወዳጇዋ እህቴ ለወይዘሪት ብስራት ። አይቸሽ ፣ ድንገተኛው ፍቅርሽ የዘወትር ሰቀቀን ሆኖብኛል ። በፍቅርሽ ወጥመድ ውስጥ ገብቼ በጉምኸርት ካራ መተፍተፍ ከጀመርኩ ውዬ አድሬአለሁ ። ዳሌሽ ፣ ጣቶችሽ ፣ ፀጉርሽ አንገትሽ ብዬ ውበትሽን ለማድነቅ አልሞክርም ። ቃላት አጥረውኝ በጅምር ከምተወው አለመሞከሩን መርጫለሁ ። ፈጣሪ ብዙ ሰዎችን መሥራት የሚችልበትን ጊዜ በአንቺ ላይ አጥፍቶአል ። ተጨንቆ ተጠቦ የሠራሽ በመሆንሽ ኩራት ይሰማሽ ። አንቺን በማፍቀሬ እኔም ኩራት ይሰማኛል ። በዓይኖችሽ ግርፍታ ከተገረፍኩ ወዲህ ፣ ዋኝቼ ከማልወጣው የፍቅር ባሕር ውስጥ ገብቻለሁ ። ከአንቺና አንቺን ከወደደው ከእኔ ሰውነት በቀር ሌላ ማየት አስጠልቶኛል ። የምበላው አይስማማኝም ፣ የሰዎች ፣ ወሬ አይጥመኝም ። ምን አለፋሽ ዘመድ የሌለው እብድ ሆኘልሻለሁ ። ይህ ሁሉ አንቺን በማፍቀሬ አንቺን በመውደዴ ነው ። ብስራት ፍቅረኛዬ እንድትሆኚ መርጬሻለሁ ። እንደማትጨክኚብኝ አውቃለሁ ። በእኔ መጨከን ያን ተጨንቆ ተጠቦ የሠራሽን አምላክ ማስቀየም ነው ። ዓይኖችሽ ብዙ በማንበብ እንዲቀሉ አልፈልግም ። መልስሽም አጭር ቢሆን ደስ ይለኛል ። ቁርጥ ያለ ። እሺ ወይም እምቢ ። ይኸን ያልኩሽ ያንቺን መልስ ማንበብ ይሰለቸኛል ብዬ አይደለም ። ብዙ በመጻፍ እኒያ አለንጋ ጣቶችሽ በብዕር እንዲዶለድሙ አልፈልግምና ነው ። በተስፋ መልስሽን እጠብቃለሁ ። ሰላምና ጤና ከአንቺ ጋር ይሁን ። ”

የፍቅርሽ ምርኮኛ

ህዳር 21 ቀን 1950 ዓ.ም.

ደጋግሜ አነበብኩት ። ጥሩ አልነበረም ። አያረካም ፣ አይስብም ። እንደገና የሚያሳዝን እኔ ከገባሁበት የፍቅር ባሕር ውስጥ እሷንም ስቦ የማስገባት ኃይል ያለው ደብዳቤ መጻፍ አለብኝ ። እንደገና መጻፍ አለበት ። ስሜትን ኰርኩሮ ፣ አሳዝኖ ፣ አሳልቆ ፣ የፍቅር ወጥመድ ውስጥ የማስገባት ኃይል ያለው ።

ነፍሳቸውን ይማረውና አባ ተገኝ መርቴሎ ፣ የቀን ሥራ ሲሠሩ ውለው ሞቅ ብሏቸው ማታ ሲመለሱ “ሴቶችን መካብ እራሴ ላይ ውጭብኝ ማለት ነው” ይሉ ነበር ። የአባ ተገኝ ንግግር ትዝ አለኝ ። እውነትም ሴቶችን መካብ አያስፈልግም ። ኩሪብኝ ፣ ዘንጭብኝ ማለት ነው ። በእራሴ ላይ አልፈርድም ። ይኸም የልብ ኩራት ሳይሰጣት አይቀርም ። ይኸንኑ እንዳለ ወስጄ አስረክባታለሁ ። ልቤን ግን ዳግመኛ አልሰጣትም ።

የህዳር ማርያም ናት ይኸን ሁሉ ጉድ የሠራችኝ ። እራሷ እንዳመጣች እራሷ ትወጣታለች ።

ሰለሞን ለማ፥ " ደብዳቤው"፥ ጉዞው እና ሌሎችም ልቦለዶች፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፥ 1979።